መልእክት አሥራ ሁለት

# ክርስቶስ ሽልማትንና ቅጣትን ይዞ መምጣቱ፣ በጨለማ ስፍራ የሚበራ መብራት፣ እና ክርስቶስ እንደ የንጋት ኮከብ ለድል ነሺዎቹ በግልና በስውር መገለጡ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 22፥12፣ 16፤ 2 ጴጥ. 1፥19

I. **“እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ”—ራእ. 22፥12፦**

ሀ. ዳግም በመምጣቱ የሚሰጠውን ሽልማቱን እናስብ ዘንድ ጌታ ማስጠንቀቂያውን ደግሞ ይናገራል፣ “በቶሎ እመጣለሁ” (3፥11፤ 22፥7)።

ለ. ጌታ በሚመጣበት ጊዜ፣ ይህ ሽልማት በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ከመነጠቃቸው በኋላ ለእያንዳንዱ አማኝ ይሰጣል—2 ቆሮ. 5፥10፤ 1 ቆሮ. 4፥5፤ ሮሜ 14፥10፤ ማቴ. 16፥27።

ሐ. በራእይ 22፥12 ላይ “ሽልማት” ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ትርጉሙ “ደመወዝ” ነው።

መ. መንግሥቱን የራሱ ለማድረግ ጌታ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ፣ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ ይሸልማል ወይም ይቀጣል፦

1. “ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ” የሚለው የጌታ ቃል ሽልማት ብቻ ሳይሆን ቅጣትም እንዳለ ስለሚያመለክት አንዳንዶች ቅጣቱን ይቀበላሉ።
2. ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በራእይ 22፥7 ጌታ “በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው” ብሎ አውጇል።
3. የራእይን ትንቢት ቃል የሚጠብቅ የተባረከ ነው ምክንያቱም ይሸለማልና።
4. በዚያን ቀን የምንቀበለው ሽልማት ዛሬ ካለን አመለካከት ጋር በእጅጉ ይገናኛል፦

ሀ. አንደኛ ቆሮንቶስ 3፥8 እንደ ድካማችን መጠን ሽልማት እንደምንቀበል ይናገራል።

ለ. በማቴዎስ 16፥27 ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ እንደ ሥራችን እንደሚሰጠን ተናግሯል።

ሠ. ዘላለማዊ ድነት ከሥራችን ጋር ምንም አይገናኝም፣ የመንግሥቱ ሽልማት ግን ከዳንን በኋላ በጌታ ሕይወት በሠራናቸው ሥራዎች ላይ ሙሉ በሙሉ የተመሠረተ ይሆናል።

ረ. መልካም ቢሆን ወይም መጥፎ፣ እያንዳንዱ የዳነ ሰው ባደረገው ነገር መሠረት በሥጋው የሠራውን ይቀበል ዘንድ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይገለጣል፤ መልካምን ያደረጉ ሽልማትን ይቀበላሉ፣ ክፉን ያደረጉ ቅጣት ይቀበላሉ—2 ቆሮ. 5፥10።

ሰ. ያለፈው ኑሯችንን፣ አካሄዳችንንና ምልልሳችንን በተመለከተ በፍርድ ወንበር ፊት ቆመን ለጌታ መልስ እንሰጣለን፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳን ራሱን እንደማይመረምር፣ ነገር ግን እርሱን የሚመረምር ጌታ እንደነበር የተናገረው ከዚህ የተነሣ ነው—1 ቆሮ. 4፥3-4።

ሸ. ከዳንን በኋላ ጌታን የምናገለግልበትና ለጌታ የምንሠራበት መንገድ ታላቅ ጉዳይ ነው።

ቀ. ጳውሎስ “ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል” ይላል—3፥14።

በ. ጌታ ተመልሶ ሲመጣ፣ ፍርድ ይኖራል፤ በዚያ ፍርድ ሽልማት ወይም ቅጣት እንደምንቀበል እርሱ ይወስናል።

ተ. ሽልማቱ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ይወሰናል፦ “መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፣ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና”—2 ቆሮ. 5፥10።

II. **“ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ”—2 ጴጥ. 1፥19፦**

ሀ. ጴጥሮስ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ያለውን የትንቢት ቃል በጨለማ ስፍራ በሚበራ መብራት ይመስለዋል፦

1. ይህ የሚያመለክተው ይህ ዘመን በጨለማ ሌሊት እንዳለ ጨለማ ስፍራ (ሮሜ 13፥12) እንደሆነና የዚህ ዓለም ሰዎች ሁሉ እየተንቀሳቀሱና እየሠሩ ያሉት በጨለማ እንደሆነ ነው።
2. የቅዱሳት መጻሕፍት የትንቢት ቃል፣ ለአማኞች እንደሚያበራ መብራት፣ የጌታ መገለጥ እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ወደ ብሩህ ቀን ውስጥ እንዲገቡ፣ ብሎም ጨለማውን ሌሊት እንዲያልፉ በመምራት

(ለአእምሯቸው መረዳት ብቻ በፊደላት የሆነ እውቀት ሳይሆን) በጨለማቸው ላይ የሚያበራ መንፈሳዊ ብርሃንን ይሰጣል።

3. ጌታ እንደ ፀሐይ ብርሃን ከመገለጡ በፊት፣ ይህ ቃል እንደ ብርሃን በእርምጃዎቻችን ላይ ሊበያራ ያስፈልገናል።

ለ. "ቀኑ እስኪጠባ" (2 ጴጥ. 1፥19) የሚለው ሃረግ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ላለው የትንቢት ቃል ማብራት በመጠንቀቅ፣ እንዲያበሩ በተደረጉ እና አብርሆት በተሰጣቸው አማኞች ልብ ውስጥ ከመውጣቱ በፊት እየወጣ ካለ የንጋት ኮከብ ጋር እንደሚጠባ ብሩህ ቀን በብርሃን የተሞላ የሚመጣን ጊዜ የሚያሳይ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው:-

1. በክህደቱ ጊዜ አማኞች እንዲህ ያለ ቀን በእነርሱ ላይ እስኪወጣ ድረስ የትንቢቱ ቃል በክህደቱ ጨለማ ላይ እንደ መብራት እንዲያበራ በዚህ ጉዳይ እየጠነቀቁ መልካም ያደርጋሉ።
2. ይህም ጌታ እንደ ሌባ በሚመጣበት በመምጣቱ ስውር ክፍል (ፓሩሺያ) እንዳያጡት የጌታን መገኘት በጥብቅ እንዲፈልጉ እና እንዲነቁ ያደርጋቸዋል፣ ያበረታታቸውማል።
3. ይህ ዘይቤያዊ አገላለጽ፣ ብርሃኑ የዚህን ዘመን ጥልቅ የጨለማ ሌሊት ለማሸነፍ በሚያበራው በጌታ እንደ የጽድቅ ፀሐይ (ሚል. 4፥2) መገለጥ (መምጣት) እንደሚጠባ ቀን (2 ጴጥ. 1፥16) የሚመጣውን ዘመን፣ የመንግሥቱን ዘመን የሚያመለክት መሆን አለበት።
4. ከዚህ አስቀድሞ፣ ከሌሊቱ እጅግ ጨለማ በሆነው ሰዓት ጌታ ለነቁና የእርሱን ውድ መገኘት ለሚፈልጉ (2 ጢሞ. 4፥8) እንደ የንጋት ኮከብ ይገለጣል (ራእ. 2፥28፤ 22፥16)።
5. እነኚህ አማኞች ወደሚጠባው ቀን ሊመራቸው በሚችለው በትንቢቱ ቃል ማብራት አብርሆት ተቀብለዋል።
6. በጨለማ ስፍራ እንደ መብራት ለሚበራው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው ቃል ከተጠነቀቅን፣ እርሱ እንደ ንጋት ኮከብ ከመገለጡ በፊት፣ ዛሬ ባለንበት በክህደቱ ጨለማ ለማብራት በልባችን የእርሱ [እንደ ንጋት ኮከብ] መውጣት ይኖረናል።

**III. "እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፣ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ"—ራእ. 22፥16:-**

ሀ. በሰማይ ባሉ ብርሃን ሰጪ አካላት፣ ብርሃናት የተመለከተው ክርስቶስ የሚያበራው የንጋት ኮከብ ነው—ቁ. 16።

ለ. ተመልሶ በመምጣቱ ክርስቶስ በአጠቃላይ ለሕዝቡ እንደሚወጣ ፀሐይ (ሚል. 4፥2)፣ ንቁ ለሆኑ አፍቃሪዎቹ ግን በተለየ መንገድ የንጋት ኮከብ ይሆናል።

ሐ. የንጋት ኮከብነቱ ለድል ነሺዎቹ ሽልማት ይሆናል:- "የንጋት ኮከብም እሰጠዋለሁ"—ራእ. 2፥28።

መ. ክርስቶስ እንደ ዳዊት ሥርና ዘር ከእስራኤልና ከመንግሥቱ ጋር የተቆራኘ ነው፣ የሚያበራ የንጋት ኮከብ መሆኑ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያንና ከንጥቀት ጋር የተቆራኘ ነው።

ሠ. የንጋት ኮከብ እጅግ ጨለማ ከሆነው ሰዓት በፊት፣ ከንጋት ቀደም ብሎ ይገለጣል።

ረ. ታላቁ መከራ የጨለማው ጊዜ ይሆናል፣ ከዚያም በኋላ የመንግሥቱ ዘመን ይመጣል፤ ይህ የሚያመለክተው በጨለማው ጊዜ፣ ይህ ዘመን ከመዘጋቱ አስቀድሞ ክርስቶስ እንደ የንጋት ኮከብ እንደሚገለጥ ነው።

ሰ. በመንግሥቱ ጌታ እንደ ፀሐይ ለሕዝቡ በገሃድ ይገለጣል፣ ከታላቁ መከራ በፊት ግን ሊነጥቃቸው ለድል ነሺዎቹ እንደ የንጋት ኮከብ በግልና በስውር ይገለጣል።

ሸ. የሚያበራው የንጋት ኮከብ ለነቁት ብቻ ይገለጣል።

ቀ. የሚያንቀላፉት አማኞች የንጋቱን ኮከብ አያዩም፤ ክርስቶስን አጠቃላይ በሆነ መንገድ እንደ ፀሐይ ብቻ ያዩታል።

በ. ረጅም ከሆነው አለመገኘቱ በኋላ ተመልሶ ሲመጣ የነቁት የመገኘቱን ትኩስነት ለመቅመስ ቅድሚያውን ያገኛሉ።

ተ. መላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚደመደመው እንደ ጸሎት በተገለጠ ለጌታ መምጣት ባለ መሻት ነው።

ቸ. በራእይ 22፥20 ያለው የዮሐንስ ጸሎት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጨረሻው ጸሎት ነው።

ኀ. "ይህን የሚመሰክር:- አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና!"—ቁ. 20።

*© 2025 Living Stream Ministry*